**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሰበር መዝገብ ቁጥር 239989

ህዳር 26 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ደጀኔ አያንሳ

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

ሐብታሙ እርቅይሁን

አመልካች፡- አቶ ጌታቸው ሮሪሳ ቀርቧል

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ብርቱካን ሁሪሳ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ፍቺና የፍቺ ውጤትን የሚመለከት የባልና ሚስት ክርክር ሲሆን ክሱ በቀረበበት የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ፣ ተጠሪ ደግሞ በተከሳሽነት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ታህሳስ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አስፈላጊ ክፍያ ተከፍሎበት መስከረም 30 ቀን 2011 ዓ.ም በተጠሪ ስም ካርታ የወጣበት የብሎክ እና ፕሎት ቁጥሩ፤ እንዲሁም ኤክስ ዋይ ኮርድኔቶቹ በክሱ ላይ የተመለከተው በሱሉልታ ከተማ ኖኖ መና አብቹ ቀበሌ 140 ካ.ሜ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ላይ ግንባታ ለመጀመር የተገዙ የግንባታ ዕቃዎች 3,400 (ሶስት ሺ አራት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

መቶ) ብር የሚያወጣ ሁለት ባጆ ድንጋይ እና ዋጋው 2,000.00 (ሁለት ሺ) ብር የሆነ 5(አምስት) ኩንታል ስምቶ ድርሻዬ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ታህሳስ 19 ቀን 2014 ዓ.ም በሰጡት መልስ በሱሉልታ ከተማ የወሌ ሉቤ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት እባትና እናታቸው በልማት ምክንያት ከይዞታቸው ስለተፈናቀሉ ለወላጆቻቸው 500 ካ.ሜ ፤ ለልጆቻቸው ደግሞ 140 ካ.ሜ በካሳ መልክ በ2011 ዓ.ም የተሰጠኝ እንጅ ከአመልካች ጋር ያገኘሁት አይደለም ፤ ካርታ ለማሰራት የተከፈለው 750(ሰባት መቶ ሃምሳ) ብርም ከግል ደሞዜ ከፍዬ ካርታ ስለተሰጠኝ እናት እና አባቴ የልማት ተነሺ በመሆናቸው በግል ያገኙትን ይዞታ የጋራ ነው በማለት የቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ የግንባታ ዕቃዎቹ የጋራ ስለሆኑ አመልካች ድርሻውን ቢካፈል ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የሱሉልታ ወረዳ ከተማ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ሰምቶ እንዲሁም ተገቢ ነው ያለውን ማጣራት አድርጎ መዝገቡን እንደመረመረው በ2008 ዓ.ም በልማት ምክንያት ይዞታቸው ለተወሰደባቸው የተጠሪ ወላጆች የቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ህዳር 14 ቀን 2010 ዓ.ም በቀበሌ በኩል ለሱሉልታ ከተማ መሬት አስተዳደር ጥያቄ ቀርቦ ግንቦት 9 ቀን 2010 ዓ.ም ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ቦታ እንዲሰጥ በከተማው ካቢኔ ተወስኖ ነሃሴ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ለሱሉልታ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ደብዳቤ ተጽፎ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቦታ በ2010 ዓ.ም መጨረሻ ላይ መሰጠቱን ከሱሉልታ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤ እንደሚያመለክት ገልጾ ፤ ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ያገኘችው በደንብ ቁጥር 182/2008 አንቀጽ 27(6) (መ) መሠረት ቤተሰቦቿ የልማት ተነሺ በመሆናቸው ምክንያት በግል ያገኘችው ቤት መሥሪያ ቦታ መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ይህን የተጠሪ ቤተሰቦች ይዞታቸው በልማት ምክንያት ተወስዶባቸው ከነበሩበት ቦታ በመነሳታቸው በምትክ ተጠሪ በግል ያገኘችውን መሬት አመልካች ልካፈል በማለት ያቀረበው ክስ የሕግ ድጋፍ የለውም በማለት በፍ.ሥ.ሥ.ሕ ቁጥር 33(2) መሠረት ክሱን ውድቅ ያደረገ ሲሆን ፤ የግንባታ ዕቃዎቹ መኖራቸው በተጠሪ አልተካደም በሚል እኩል እንዲካፈሉ ወስኗል፡፡ ጉዳዩን አመልካች ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ የተመለከተው የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን ክፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች እና ተጠሪ ሚያዝያ 21 ቀን 2011 ዓ.ም ተጋብተው በትዳር ውስጥ እያሉ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለአርሶ አደር ቤተሰቦች እንዲሰጥ ግንቦት 9 ቀን 2010 ዓ.ም በካብኔ ተወስኖ በ2010 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ለተጠሪ ተሰጥቶ 2011 ዓ.ም ካርታ የተሰራበት መሬት የጋራ መሆን ሲገባው የተጠሪ የግል ይዞታ ነው መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል፡፡ ተጠሪ በውሳኔው ባለመስማማት ባቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው ይግባኝ ሰሚው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከተጠሪ ወላጆች በ2007 እና 2008 ዓ.ም በልማት ምክንያት ለተወሰደባቸው መሬት በ2009 ዓ.ም ለባለይዞታዎቹ እና ቤተሰቦቻቸው የቤት መስሪያ እንዲሰጥ ግራ ቀኙ ጋብቻ ከመመስረታቸው ሚያዝያ 21 ቀን 2010 ዓ.ም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

በፊት እንዲሰጥ ውሳኔ ተላልፎ ተጠሪ ቤተሰቦቿ የልማት ተነሽ በመሆናቸው በደንብ ቁጥር 182/2008 ቁጥር 27(1) እና (6) መሠረት ያገኘችው ይዞታ በክልሉ የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 አንቀጽ 73 መሠረት የግሏ ሆኖእያለ ግራ ቀኙ ጋብቻ ከመሠረቱ በኋላ በ2011 ዓ.ም በተጠሪ ስም የይዞታ ማረጋገጫ ስለተሰጠ ብቻ የጋራ ነው መባሉ አግባብ አይደለም በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔን ሽሮ የሱሉልታ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን ያፀና ሲሆን ፤ አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ጉዳዩን የተመለከተው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት ተጠሪ አከራካሪውን መሬት ያገኘችው የወላጆቿ ይዞታ በ2008 ዓ.ም በልማት በመወሰዱ ምክንያት በመሆኑ መብቱን ያገኘችው የቤተሰቦቿ መሬት በልማት ምክንያት በተወሰደበት ጊዜ በ2008 ዓ.ም እንጅ መሬቱ እንዲሰጣት ውሳኔ በተላለፈበት በ2010 ዓ.ም ባለመሆኑ እና መብቱን ባገኘችበት ጊዜ ደግሞ ግራ ቀኙ ጋብቻ ስላልመሰረቱ ተጠሪ በግል ባለመብት ሆኖ ካርታ በስሟ ባገኘችው ባዶ መሬት ላይ ያደረገው አንዳች አስተዋጽኦ ሳይኖር አመልካች ልካፈል ይገባል በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት ማጣቱ ተገቢ ነው በማለት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን በአብላጫ ድምጽ አጽንቷል፡፡

የሰበር ቅሬታው የቀረበውም ይህን ውሳኔ በመቃወም በሰበር ለማስለወጥ ሆኖ የቅሬታው ይዘት በአጭሩ፡- በአመልካች እና ተጠሪ መካከል ጋብቻ የተመሰረተው ሚያዝያ 21 ቀን 2010 ዓ.ም ሆኖ በትዳር ውስጥ እያለን ቦታውን ለማግኘት አስፈላጊ የሆነውን ክፍያ ከትዳር ወጪ አድርገን ከከተማ አስተዳደሩ በተጠሪ ስም መስከረም 30 ቀን 2011 ዓ.ም ካርታ በተሰጠን ይዞታ ላይ ቤት ለመስራት ድንጋይ አውርደን እያለን ትዳራችን መፍረሱ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ከቤተሰቦቿ በስጦታ ያላገኘችውን መሬት የግሏ ነው ተብሎ በሥራ ላይ ባለው መመሪያ ለባልና ሚስት አንድ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ብቻ ስለሚሰጥ አመልካች ከዚህ በኋላ ከሱሉልታ ከተማ ሌላ መሬት እንደማላገኝ እየታወቀ በኦሮሚያ ልዩ ዞን የፊንፊኔ ዙሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሻሩ ስህተት ነው በማለት ውሳኔ እንድፀና ጠይቀዋል፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በትዳር ውስጥ የተገኘ ንብረት ለተጠሪ ብቻ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት መጣራት አለበት ትብሎ ተጠሪ በጽሑፍ መልስ እንዲሰጡ ታዘው ተከታዩን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪ ሚያዝያ 16 ቀን 2015 ዓ.ም በተፃፈ መልስ፡- ከአመልካች ጋር ትዳር ከመመስረታቸው በፊት በ2007 እና 2008 ዓ.ም የወላጆቻቸው የሆነ ይዞታ በልማት ተፈልጎ ስለለቀቁ በደንብ ቁጥር 27(1) እና (6) መሠረት ለወላጆቻቸው 500 ካ.ሜ ሲሰጥ በውቅቱ ተጠሪም ለአቅመአዳም ደርሰው ስለነበረ 140 ካ.ሜ በግል እንዲሰጣቸው ተወስኖ ይዞታው የማስተላላፍ ሂደቱ በተለያየ ምክንያት ሲጓተት ቆይቶ በ2009 ዓ.ም መሬት በምትክ እንዲያገኙ ውሳኔ ተላለፎ ካርታው በ2011 ዓ.ም በግል ለተጠሪ የተሰጠ እንጅ ግራ ቀኙ በጋራ ጥረታችን ያፈራነው ወይንም ተጠሪ የግል ንብረታቸውን ሸጠው በግብይት የተገኘ ንብረት ባለመሆኑ አመልካችን የማይመለከት ሆኖእያለ አመልካች ንብረቱ ለተጠሪ የተላለፈው ጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ብቻ በመሆኑ የጋራ እንዲባልላቸው ያቀረቡት ክስ የክልሉ ቤተሰብ ሕግ መሠረት ያደረገ ከመሆኑም በላይ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካች የጠቀሱት የሰበር አቤቱታ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው በለመሆኑ ለተፈናቃይ የተሰጠ ቦታ ስለማይመለከታቸው ለሰበር አቤቱታው መሠረት የሖነው ውሳኔ የሚነቀፍ ስላልሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቀርበዋል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለ መልኩ የተመለከተዉ የግራ ቀኝ ክርክር እና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ሲል የያዘዉን ጭብጥ እና በስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አዋጅ ቁጥር 1/1987 አንቀጽ 40(4) አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘት እና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብት እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለመያዝ የወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 የከተማ ቦታን የማስለቀቅ ሥልጣን ያለው አካል ከቦታው ላይ ለሚነሳው ንብረት ተገቢው ካሣ በቅድሚያ እንዲከፈል በማድረግ የከተማ ቦታን ለህዝብ ጥቅም ሲባል ማስለቀቅ እንደሚችል፤ በዚህ እርምጃ ተነሺ የሚሆን ሰው በክልሉ ወይንም በከተማ አስተዳደሩ የሚወሰን ምትክ ቦታ እንደሚያገኝ አንቀጽ 12(2) እና 26 ይደነግጋል፡፡ የመሬት ባለይዞታነት መብት በጊዜ የማይገደብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ሊቋረጥ የሚችለው መሬቱ ለበለጠ የህዝብ ጥቅም ሲፈለግ ብቻ መሆኑን ፤ በይዞታው የመጠቀም መብቱ ለበለጠ የህዝብ ጥቅም የተወሰደበት አርሶ አደር ፤ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አዳር ለንብረቱና በዚህ ምክንያት ላጣው ጥቅማጥቅም አስቀድሞ ካሣ የማግኘት መብት እንዳለው የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጣቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 6(1), 6(10) እና 6(11) ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡ በልማት ወይንም በመልሶ ማልማት ምክንያት ይዞታቸውን ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ለሚለቁ አርሶ አደር ፤ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አዳር የምለቁትን የመሬት መጠንና የከተማውን እስታንዳርድ መሠረት አድርጎ 500 ካ.ሜ ወይንም ከዚያ በታች የቤት መሥሪያ ቦታ በኪራይ የሚያገኙ መሆኑን ፤ እንዲሁም ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ከባለይዞታው ጋር የሚኖሩ ከከተማው የመኖሪያ ቤት የሌላቸው የልማት ተነሺ አርሶ አደር ፤ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አዳር ልጆች በከተማው እስታንዳርድ መሠረት የቤት መሥሪያ ቦታ እንደሚያገኙ የኦሮሚያ የከተማ መሬቶችን በሊዝ ለማስተዳደር ተሻሽሎ የወጣው ደንብ ቁጥር 182/2008 አንቀጽ 27(1), (6), (ለ) እና (መ) ድንጋጌ ያስረዳል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች እና ተጠሪ ትዳር የመሰረቱት ሚያዝያ 21 ቀን 2010 ዓ.ም ሲሆን የተጠሪ ቤተሰቦች ከዋሌ ሉቤ የነበራቸው ይዞታ በ2008 ዓ.ም በልማት ስለተወሰደባቸው የቤት መስሪያ ቦታ እንዲሰጣቸው ህዳር 14 ቀን 2010 ዓ.ም በቀበሌ በኩል ለሱሉልታ ከተማ መሬት አስተዳደር ጥያቄ ቀርቦ በከተማው ካቢኔ ግንቦት 9 ቀን 2010 ዓ.ም ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ቦታ እንዲሰጥ የተላለፈው ውሳኔ ነሃሴ 23 ቀን 2010 ዓ.ም ለሱሉልታ ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ደብዳቤ ተጽፎ አከራካሪው በክሱ ላይ አዋሳኞቹ

የተመለከተው 140 ካ.ሜ የከተማ ቦታ በ2010 ዓ.ም መጨረሻ ላይ መሰጠቱን እና ተጠሪ በ2011 ዓ.ም ካርታ ያገኙ መሆኑ ከሱሉልታ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት የካቲት 30 ቀን 2014 ዓ.ም እንዲሁም መጋቢት 5 ቀን 2014 ዓ.ም የተፃፈ ደብዳቤዎች እና ለተጠሪ የተሰጠው ካርታ ያመለክታል፡፡ ተጠሪ የቤት መሥሪያ ቦታውን የማግኘታቸው ምክንያት የወላጆቻቸው የልማት ተነሽ በመሆናቸው ሆኖ ፤ የቤት መሥሪያ ቦታው እንደ ካሣ መሬቱ ከመለቀቁ አስቀድሞ የሚሰጥ መሆኑ በሕጎቹ ላይ በግልጽ አልተመላከተም፡፡ ተጠሪ የወላጆቻቸው መሬት በልማት በተወሰደበት ጊዜ ማለትም በ2008 ዓ.ም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት የሞላ መሆኑ ፣ የይዞታ መሬታቸው ከተወሰደባቸው ወላጆቻቸው ጋር የሚኖሩ እና በከተማ ውስጥ የመኖሪያ ቤት የሌላቸው መሆኑ ተረጋግጦ የልማት ተፈናቃይ ቤተሰቦችን መልሶ ለማቋቋም ታስቦ አከራካሪው ይዞታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ የቤት መስሪያ ቦታው የልማት ተነሺው አርሶ አደር ፤ አርብቶ አደር ወይም ከፊል አርብቶ አዳር ልጆች የሚሰጥበት ጊዜ በሕጉ በግልጽ ባይጠቀስም የሕጉ ዓላማ የልማት ተነሺ ቤተሰቦች በልማት ምክንያት አስቀድሞ የሚኖሩበት አከባቢ ስለምነሱ እንዳይበተኑ መልሶ ለማቋቋም በመሆኑ ፤ የቤት መሥሪያ ቦታው በወቅቱ ባለመሰጠቱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ትዳር ከመሰረቱ በኋላ በልማነት ተነሺ ልጅነታቸው አስቀድሞ ከነበሩበት ቦታ ስለተፈናቀሉ መልሶ ለማቋቋም ዓላማ በሕጉ የተመለከተውን መስፈርት አሟልተው በግል ያገኙትን የቤት መሥሪያ ቦታ አመልካች ሊጋራ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክርክር የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 69/1995 አንቀጽ 73 እንዲሁም በሰበር መዝገብ ቁጥር 65708 (በቅጽ 13 እንደታተመው) የተሰጠውን አስገዳጅ ውሳኔን የሚቃረን ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**ዉሳኔ**

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚው ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 405399 ህዳር 06 ቀን 2015 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥነ - ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 ቁጥር 9(1/ለ) መሠረት ፀንቷል፡፡

2. በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ውሳኔ አግኝቶ ስለተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## የሃሳብ ልዩነት

ስሜ በተራ ቁጥር አምስት ላይ የተሰየምኩት ዳኛ ከአብላጫው ሃሳብ የተለየሁበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

ከክርክሩ እንደተገነዘብኩት በሱሉልታ ከተማ ኖኖ መና አብቹ ቀበሌ 140 ካሬ ሜትር ቦታ የተፈራው ወይም የተገኘው አመልካችና ተጠሪ በትዳር ግንኙነት በነበሩበት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ ቦታው የተገኘው ተጠሪ የልማት ተነሺ ልጅ በመሆናቸው ምክንያት በኦሮሚያ ክልል የከተማ መሬት የሊዝ ደንብ 182/2008 መሰረት ነው፡፡ ይህም የንብረት መብቱ ምንጭ ህግ መሆኑን ያሳያል፡፡ ተጠሪ ከህግ ሆነ ከውል በመነጨ ሁኔታ በትዳር ላይ እያሉ ንብረት ካፈሩ ወይም የንብረት ባለመብት ከሆኑ ንብረቱ የጋራ ወይስ የግል ንብረት ይሆናል የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው እና የሚገዛው በቤተሰብ ህግ እንጂ በከተማ መሬት የሊዝ ህግ መሰረት አይደለም፡፡ ሊዝ ደንቡ ስለባልና ሚስት ንብረት ውጤት የማይደነግግ ከመሆኑም በላይ ስለባልና ሚስት የንብረት ውጤት ቢደንግግ እንኳን የኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ የሆነውን አዋጅ ቁጥር 69/1995 እና 83/1996 ተቃርኖ ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡

በኦሮሚያ ክልል የቤተሰብ ህግ አንጻር 78 መሰረት ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ ያፈሯቸው ንብረቶች በሙሉ የጋራ ሀብት እንደሚሆኑ ተመልክቷል፡፡ ክርክር ያስነሳው ንብረት የተፈራው ግራ ቀኙ ከተጋቡ በኋላ በመሆኑ ንብረቱ የጋራ ንብረት ነው፡፡ በቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 73 እና 74 መሰረት የግል ንብረት የሚሆነው ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ከጋብቻ በኋላ አንደኛው ተጋቢ በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘው ንብረት እና የግል ንብረት የሆነው ሲለወጥ/ለውጡም በፍርድ ቤት ሲጸድቅ/ ስለመሆኑ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ማዕቀፍ ውጭ በጋብቻ የተፈራ የግል

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የሚሆንበት አግባብ በቤተሰብ ህጉ የሌለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ክርክር ያስነሳው ቦታ የተጠሪ የግል ንብረት ስለሆነ አመልካች ሊካፈሉ አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 34 መሰረት ባልና ሚስት እኩል መብት ያላቸው መሆኑን የደነገገውን የተላለፈ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !